**አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች የቤተሰብ ህይወት ትምህርት ላይ የወላጆች በምርጫ የማስተማር ፎረም - 7ኛ ክፍል**

የተማሪው ስም : ________________________________ ስልክ ቁጥር: ___________________
የአስተማሪው ስም: ________________________________ ቀን : ______________________

እኔ እዚህ ያለሁት ከተዘረዘሩት አላማዎች ውስጥ ልጄ እንዳይሳተፍ የምፈልግበትን ምርጫ እንዳደርግ ነው። ልጄ እንዳይሳተፍ በማደርግባቸው አላማዎች ላይ፣ ልጄ ያለምንም ተፅእኖ አማራጭ አሳይመንቶች እንደሚሰጡት ተረድቻለሁ። ልጄ አሳይመንት በሚሰራበት እና ለአሳይመንቱ ውጤት በሚሰጥበት ወቅት፣ በትምህርት ቤቱ ህጎች እና ፖሊሲዎች መመራት እንደሚጠበቅበት ተረድቻለሁ።

<u>**አቅጣጫዎች:**</u> እባክዎ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አላማዎች ላይ ልጅዎ እንዳይሳተፍበት የሚፈልጉትን ነገር ካለ ምልክት ያድርጉበት።

___ **7.1 ተማሪው በቤተሰቡ ውስጥ የሚኖረውን የራሱን ድርሻ እንዲሁም ግንኙነቱን ይለያል።**
<u>መግለጫ</u>: የዚህ ይዘት የሚያካትተው ግላዊ መስተጋብሮችን፣ የተግባቦት ክህሎትን፤ ስሜታዊ፣ አካላዊ እና ስነ-አዕምሮአዊ የምርምር ፍላጎቶችን የማሳካት መንገድ፤ እንዲሁም ተማሪው ለቤተሰቡ የሚኖረውን አስተዋጽኦ ነው። ተማሪዎች እንደአስፈላጊነቱ የራስን ፍላጎት መስዋት በማድረግ የቤተሰብን ግብ የመደገፍን አስፈላጊነት ይማራሉ።

___ **7.2 ተማሪው ፆታዊ መገለጫ የሆኑ የአካል ክፍሎችን እድገት ይለያል፤ በተጨማሪም ስሜታዊና ማህበራዊ እድገቱ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ይገነዘባል።**
<u>መግለጫ</u>: የዚህ ትኩረት የሚሆነው የጉርምስና ዕድሜ መጀመርያ ላይ ያሉ ባዮሎጂያዊ እና አካላዊ ለውጦች ላይ ይሆናል። ተጨማሪ ትኩረት የሚሰጣቸውም ጉዳዮች 2ኛ ደረጃ ስነ-ፆታዊ መገለጫ የሆኑት የአካል ዕድገት፣ የመራቢያ አካላት ለውጥ፣ የሆርሞኖች መመንጨት፣ የወር አበባ አጀማመር፣ እንዲሁም ለግብረ ስጋ ምላሽ ስሜቶች ላይ ነው። መመርያው ራስን በደንብ በማሳወቅና ስለ የወር አበባ፣ ድንገተኛ የብልት መገተር፣ በምሽት ጊዜ የሚኖር መርጨት፣ ሴጋ፣ እና የዕድገት ፍጥነት ልዩነት ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ወደፊት የሚመጣን ጭንቀት ይቀንሳል።

___ **7.3 ተማሪው አካላዊ ደስታ(ፍቅር) ግዴታ በ ወሲባዊ መንገድ ሳይሆን ጓደኝነትን በመግለጽ ፣ በክብረ በዓላት እና በሚወድ ቤተሰብ ሊገለጽ እንደሚችል ይረዳል።**
<u>መግለጫ</u>: ተማሪው ትክክለኛ የሆነ አገላለጽ ለስሜታዊ፣ አካላዊ፣ እንዲሁም ስነ-ልቦናዊ ጤና ያለውን አስፈላጊነት ይረዳል። ተማሪው ተገቢ የሆነና ተገቢ የልሆነ አካላዊ ፍቅርን ይለያል። ጎጂ የሆኑ ግንኙነቶች መገለጫዎችም ይዳሰሳሉ።

___ **7.4 ተማሪው ወሲባዊ ባህርይዎች ሆን ተብለው የሚፈጠሩ ውሳኔዎች እነደሆኑ ይለያል፤ ማለትም ከጋብቻ በፊት የሚፈፀም ወሲብ፣ ጎጂ የሆኑ ግንኙነቶች፣ ተገቢ ያልሆኑ ወሲባዊ ግንኙነቶች፣ ‹አይሆንም የማለትን አስፈላጊነት፣ እና ትክክለኛ ግንኙነቶች የጋራ በሆነ መከባበር ።**
<u>መግለጫ</u>: ወሲባዊ ስሜቶች ሚከሰቱ እና ሚጠበቁ ናቸው። ሆኖም ግን ሁልጊዜ ስነ-ባህርይ ውስጥ መካተት አይኖርባቸውም። መመርያው በአስፈፈላጊነት እና በምኞት መሀል ያለውን ልዩነት፣ ለራ ሃሳብ ስለመቆም ክህሎት፣ ችግር ወይም ግጭት አፈታት፣ እና ሌሎች አማራጮች ለላይ ማብራሪያዎችን የያዘ ነው። ተማሪዎች የመቃወም ክህሎትን ይማራሉ እንዲሁም በተግባር ይለማመዳሉ። ጎጂ የሆነ ግንኙነት መገለጫዎች ማለትም፤ የአልኮል ወይም የሌሎች ንጥረ-ነገሮች ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም፤ እንዲሁም ተገቢ

ያልሆነ የተንቀሳቃሽ ስልክና በይነ-መረብ የመሳሰሉ የኤሌክትሮኒክ ውጤቶች አጠቃቀም ይታዩበታል። በተጨማሪም የአፍላ ዕድሜ እርግዝና ውጤቶች፣ በግብረ-ስጋ ግንኙነት ተላላፊ ስለሆኑ በሽታዎች፣ እንዲሁም ወሲባዊ እንቅስቃሴን ስለማዘግየት ጥቅሞች ለውይይት ይቀርባሉ።

___ **7.5 ተማሪው ስነ ወሲብን የተመለከቱ በማሕበረሰቡ ውስጥ ያሉ መልክቶችን ይለያል።**
<u>መግለጫ</u>: መምህሩ ተማሪው ወሲባዊ ይዘት ያላቸውን ማስታወቂያዎችን፣ ሙዚቃዎችንና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን፣ ፊልሞችን የታተሙውጤቶችን እና፣ በየግድግዳው ያሉ ፅሁፎችንና ስዕሎችን ለይቶ እንዲያውቅ ያግዘዋል። ተማሪዎች ፆታን መሰረት ስላደረጉ የተሳሳቱ አመለካከቶች እናወሲባዊ ብዝበዛ ለይቶ ያውቃል። በዚህም የራሳቸወ3ን ግምገማ ካደረጉ በሁዋላ ያገኙት አሉታዊ ተፅዕኖ ላይ ምላሽ እንዲሰጡና ጊዜያቸውን ጠቃሚ ያልሆነ ይዘት ያላቸው የመገናኛ ብዙሃን ውጤቶችን በመመልከት ከማጥፋት ይልቅ አወንታዊ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ ይበረታታሉ።

___ **7.6 ተማሪው በይነ መረብን(ኢንተርኔት) የተመለከቱ የደህንነት ሁኔታዎችን ይመረምራል።**
<u>መግለጫ</u>: ይህ መመርያ አጥቂ ሰዎች እንዴት ኢንተርኔትን ተጠቅመው ህጻናትን እንደሚበዘብዙ፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን እነደሚያካሂዱ፣ እነዲሁም ተገቢ ያልሆነ ይዘት ያላቸው መልክቶች እንዴት እነደሚለጠፉ ከዚህ በተጨማሪም የግል መረጃቸውን እንዴት ከጥቃት እነደሚከላከሉ ይገልጻል። ተማሪዎች እንዴት አጥቂዎች ኢንተርኔትን ተጠቅመው ተጠቂዎችን አባብለው በህገወጥ መንገድ እነደሚያዘዋውሩ እና በሚዲያው ለይ የሚለጠፉ መልክቶች እንዴት ተማሪዎችን ተጋላጭ እነደሚያደርጉ ይረዳሉ። የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች እንዴት ራሳቸውን ከጥቃት መጠበቅ እንደሚችሉና የአዋቂ ድጋፍ ሲያስፈልጋቸው እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ መንገዶችን ይዘረዝራሉ።

___ **7.7 ተማሪው የቅድመ አፍላ ዕድሜ እና የአፍላ እድሜ ወሲባዊ ግንኙነት ውጤቶችን ይለያሉ።**
<u>መግለጫ</u>: ይህ መመርያ ትኩረቱን የሚያደርገው ኤ. አይ. ቪን ጨምሮ በግብረ ስጋ ግንኙነት ስለሚተላለፉ በሽታዎች፣ ስለ ፔልቪክ ኢንፍላማቶሪ ዲዚዝ፣ ስለ ማህፀን ካንሰር፣ ስላለተፈለገ እርግዝና እንዲሁም ስለማንነት ክብር፣ ጥፋተኝነት ስሜትና ጭንቀት ላይ ይሆናል። በተጨማሪም ከጋብቻ በፊት ስለሚኖር ወላጅነት እና ወሲባዊ ግንኙነት ስሜታዊ፣ ስነልቦናዊና ኢኮኖሜያዊ መዘዞች ይመለከታል። ተማሪዎች ስለራሳው አወንታዊ ማንነት እነዲያውቁ እና ከአደጋ አጋላጭ ባህርይዎች እንዲቆጠቡ ይታገዛሉ። እንዲሁም ወሲባዊ እንቅስቃሴን በማዘግየት የሚገኙ አወንታዊ ውጤቶችንና ነጻነቶችንም ይማራሉ።

___ **7.8 ተማሪው የአፍላ ዕድሜ እርግዘና ውጤቶችንና ወሲባዊ እንቅስቃሴዎችን እስከጋብቻ የማቆየት ጥቅሞችን ይዘረዝራል።**
<u>መግለጫ</u>: በዚህ መመርያ ከዚህ ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች የተመለከቱትን ስለ እርግዝና እና ወሊድ በድጋሚ ማየት እና በወጣት(አፍላ) ወላጆች እና ቤተሰቦቻቸው ላይ የኖረውን ስሜታዊ፣ አዕምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ማሕበራዊ፣ እና ምጣኔ ሃብታዊ ተፅዕኖ ይዳሰሳሉ። የአፍላ ዕድሜ እርግዝና በተማሪዎች የዕድሜ ልክ ግብ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ይታያል። ከመውለድ በፊት ፅኑ ግንኙነት ውስጥ ወይም ትዳር ውስጥ የመሆን ጠቀሜታ እና በቤተሰብ ፣ በሚወለደው ልጅ ብሎም በማህበረሰብ ላይ የሚኖረው ተጽዕኖም አብሮ ይታያል።

___ **7.9 ተማሪው የእርግዝና ምልክቶችን ይገልጻል።**
<u>መግለጫ</u>: መመሪያው አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ለውጦችን እና ፈጣን የሆነ በጤና ተቐም የእርግዝና ምርመራ ማድረግ ስኬታማ ለሆነ እርግዝና ያለውን አስተዋጾ ያብራራል። በማሕበራሰቡ ያሉ የመመርመር ወይም የመረጃ መስጠት አቅሞች ተለይተዋል።

___ **7.10 ተማሪው ስለ ቤተሰብ ዕቅድ ዕውቀት እና ሃላፊነት ያዳብራል።**
መግለጫ: በዚህ ውስጥ የሚታዩት የቤተሰብ ዕቅድ አስፈላጊነት፣ በቤተሰብ ዕቅድ ወቅት ከግምት መግባት ስላለባቸው ነጥቦች፣ ማህበራዊ ጉዳዮች እንዲሁም የእርግዝና መከላከያ መንገዶች ናቸው።

___ **7.11 ተማሪው ወሲባዊ ጥቃት፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውርንና ወሲባዊ ማባበልን እንዴት እንደሚከላከልና እንደሚጠቁም መንገዶችን ይዘረዝራል።**
መግለጫ: ጥቃትንና ማባበልን የማስተናገጃ እነዲሁም የመከላከያ መንገዶች ተጠቅሰዋል። ተገቢው ተመልካች በሌለበት የሚያውቁት ሰው መኪናም ሆነ ቤት ውስጥ አለመሆነን ጨምሮ ለጥቃት አጋላጭ የሆኑ ሁኔታዎችን መከላከል። ተማሪዎች ተገቢ የሆነ ኢነተርኔት አጠቃቀምና የፅሁፍ መልክት አላላክን ይማራሉ። በኢነተርኔትም ሆነ በአካል አጥቂ የሆኑ ሰዎች አቀራረብ እና ባህርይ ይማራሉ። የህገ ወጥ ሰዎች ዝውውር መገለጫዎች፣ የመቆጣጠሪያ መንገዶቹና እነዴት ለአዋቂ መጠቆም እንዳለባቸው ይመለከታሉ። የጥቃት ሰለባ ለሆኑ ሰቆች ማሕበረሰቡ ውስጥ ስለሚገኙ ሃብቶች ይለያሉ።

___ **7.12 ተማሪው እንደ ኤች.አይ.ቪ. ያሉ በ ግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን ምክንያት፣ ምልክቶች፣ መተላለፊያ መንገዶች፣ህክምና እና መከላከያ ምገዶችን ይለያሉ።**
መግለጫ: ርዕሰ ጉዳዩ እነደ ኤች.አይ. ቪ.፣ ክላሚዲያ፣ ጄኒታል ሄርፕስ፣ ጎኖሪያ፣ አች.ፒ፣ቪ. እና ሲፊሊስ የመሳሰሉ በሽታዎች መነሻ፣ ምልክቶች፣ ህክመና፣ መተላለፊያ መንገዶች፣ መከላከያ መንገዶች ይዳሰሱበታል። በተጨማሪም የተሳሳቱ አስተሳሰቦች ይታረሙበታል። እነደ ስለታም ነገሮች መጋራት፣ ግዴለሽ የሆነ የንጥረ ነገር አጠቃቀምና ጥንቃቄ የጎደለው የግብረስጋ ግንኙነትን የመሳሰሉ አጋላጭ ሁኔታዎች ይታያሉ። የማህበረሰቡ የመመርመርና የህክምና የህክምና አቅም እነዚህን በሽታዎች በተመለከተ ይለያሉ።

___ **7.13 ተማሪው ከጓደኝነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ይመለከታል።**
መግለጫ: ተማሪው ይህን የሚያከናውነው ስለ ጓገኝነት አይነት እና እነዴት በሕይወት እድገት ደረጃዎች ውስጥ ጓደኝነት እነደሚለወጥ በመለየት ነው። ተማሪው ጤናማ ስለሆኑ እና ጤናማ ስላልሆኑ ግንኙነቶች ይለያሉ። ግላዊ እና የሌሎችን ነጻነት እና መታለፍ የሌለባቸውን መስመሮች ማክበራቸውን የሚያረጋግጡ መንገዶች ለተማርቹ ይተዋወቃሉ።

___ **7.14 ተማሪው በጉርምስና ወቅት ስለሚኖር የአቻዎቹ ድርሻ እና ስለ ፍቅር ግንኙነት ምንነትና አስፈላጊነት ይረዳል።**
መግለጫ: ርዕሱ ስለ ጓደኝነት ሁኔታዎች፣ ከአቻ ቡድን ጋር ስለሚኖር አወንታዊ ተሳትፎ አያበረታታ የፍቅር ግንኙነትን ይገልጻል። በቡድን መገናኘትን እንደመልካም የፍቅር ሕይወት መጀመርያ መንገድ በመቅረብ፣ አግባብ የሆነና አግባብ ያልሆን የፍቅር ግንኙነት በህርያትን በማሳየት፣ መልካም የሆኑ አዕምሮአዊ ጤና ተግባራትን በመጠቀም የፍቅር ግንኑነት ውስጠረ ስላሉ ሃላፊነቶች መወጣት ይገልጻል።

___ **7.15 ተማሪው የተለያዩ የዘርና የብሔረሰብ ቡድኖች የቤተሰብ ሕይወት ላይ ያላቸውን አስተዋጽኦ ይለያል**
መግለጫ: ርዕሱ የሚያካትተው ዘር ለቤተሰብ ማንነት አስፈላጊነት እና ከዘር ጋር የተያያዙ የተሳሳቱ አመለካከቶች ላይ ነው። ትኩረቱ የሚሆነው ልዩነትን ማክነበር እና ማድነቅ ላይ ይሆናል።

___ **7.16 ተማሪው የተለያዩ ሃሳቦችን የማዳመጥና የሃሳብ ልዩነትን የማክበር ችሎታውን ያዳብራል።**

መግለጫ: አወንታዊ የተግባቦት ክህሎትን በማዳበር መልካም ግንኙነቶችን መገንባት እና በቤተሰብ እና ማህበረሰብ ውስጥ ላሉ የተለያዩ ሀሳቦች እውቅና መስጠትን ያካትታል።

**ትምህርት ቤታችሁ በወሰነው ቀን መሰረት ይህንን ቅፅ በመሙላት ለርእሰ-መምህሩ እባክዎን ያስረክቡ**

የወላጅ/የአሳዳጊ ፊርማ: ____________________________________________ ቀን: ___________